# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ግዥ ልዩ የአፈፃፀም መመሪያ

# ቁጥር 222/2013

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በወቅቱና ደህንነቱ በተጠበቀ አኳኋን መፈጸም አስፈላጊ በመሆኑ፣
ኤጀንሲው ሀገራዊ በሆኑ የኢንፎርሜሽን ኔትወርክና የኢንፎርሜሽን ደህንነት ሥራዎች ላይ የሚሰራ ተቋም በመሆኑ ለስራው የሚያስፈልጉት በአብዛኛው ከውጭ ሀገር የሚገዙ ዕቃዎች በተለየ ጥንቃቄ መግዛት ስለሚያስፈልጋቸው እና እንደ ግብአት የሚጠቀምባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች የቴክኖሎጂ ምንጫቸው፣ የጥራት ደረጃቸው፣ ሞዴልና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች በግዥ ሥርዓቱ ምክንያት ለሌላ አካል መተላለፍ ሳይኖርባቸው ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ግዥዎችን መፈፀም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥ ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 3/2/ሀ/ እና 78/2/ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 8 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ግዥ ልዩ የአፈጻጸም መመሪያ" ቁጥር 222/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

2.1 የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

ሀ/ "ኤጀንሲ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፡፡

ለ/ "የአባልነት ምዝገባ" ማለት ኤጀንሲው በድረ-ገጽ አማካኝነት የደንበኝነት አባልነት ክፍያ በመክፈል ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር ስምምነት በመፈፀም ልዩ ልዩ የኤሌክትሮኒክ ፅሁፎችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከሄድ ምዝገባ ነው፡፡

ሐ/ "የአባልነት ምዝገባ ክፍያ" ማለት ኤጀንሲው በአባልነት ለመመዝገብ ስምምነት ሲፈፅም ለአቅራቢው የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

መ/ "የትብብር ስምምነት" ማለት የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማድረግ ኤጀንሲው ከአቅራቢው ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው፡፡

ሠ/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በፌደራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌዴራል የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የሥራ ባህርይ አንፃር ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ ለሚገባቸው በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ለተመለከቱ ግዥዎች ብቻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## በኤጀንሲው የሚፈፀሙ ልዩ ግዥዎች

### 4. ለኤጀንሲው የተፈቀዱ ልዩ ግዥዎች አፈፃፀም

በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በአንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ 1 የመንግስት መ/ቤቶች ግዥን ከአንድ አቅራቢ መፈፀም ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎች ከተደነገገው በተጨማሪ ኤጀንሲው፡-

4.1 ከመረጃ መረብ ደህንነት ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ከአንድ አቅራቢ መፈፀም ይችላል፡፡

4.2 ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ 1 በጠቅላላ አነጋገር የተገለፀው ሳይገደብ ኤጀንሲው፡-

ሀ/ ለምርምር ሥራው የሚያስፈልጉትን ግብአቶች ግዥ ከመረጃ መረብ ወይም ከሌላ ምንጭ በሚያገኘው መረጃ መሰረት መፈፀም፣

ለ/ ለኤጀንሲው የደህንነት ሥራ የሚጠቅሙ በአለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ የምርምር ተቋማት የሚገኙ የምርምር ፅሁፎችን ከመረጃ መረብ ምንጮች ለማግኘት የአባልነት ምዝገባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስፈላጊውን የአባልነት ምዝገባ ክፍያ በመክፈል አገልግሎቱን ማግኘት፣

ሐ/ ለኤጀንሲው የደህንነት ሥራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ከምንጫቸው መግዛት ወይም በሶፍትዌሮቹ የመጠቀም መብትን መግዛት፣

መ/ ለስራ የሚያስፈልጉትን የምክር አገልግሎቶች ወይም የቴክኖሎጂ ውጤቶች በቀጥታ ከአምራቹ ወይም በአምራቹ ፈቃድ ከተሰጠው አከፋፋይ መግዛት፣

ሠ/ ከታወቁ አለም አቀፍ የምርምር ተቋማት ጋር የትብብር ስምምነት በማድረግ ለሚያከናውናቸው የምርምር ሥራዎች የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች መግዛት ይችላል፡፡

4.3 ከኤጀንሲው የደህንነት ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች የኤጀንሲው ግዥዎች አፈፃፀም በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌደራል የመንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ይመራል፡፡

### 5. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ______________ ዓ.ም

ሶፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚልማት
ሚኒስትር